# በሥዕል የተደገፈ የዕባዳዎች አፈጻጸም ፍቅህ

## የእስላም ዝርዝር ሕግጋት ትምህርት በቀላል አቀራረብ

ጦሃራ | ሶላት | ጾም | ዘካ | ሐጅ



ዶክተር ዐብዱላህ ባሀማም

ተርጓሚ

ሙሐመድ ጀማል ሙኽታር

## ነጃሳዎችን የሚመለከቱ ብያኔዎች

https://www.al-feqh.com/am



# 2 ነጃሳዎችን የሚመለከቱ ብያኔዎች

## ማውጫ


- የነጃሳ ትርጓሜ
- የነጃሳ ዓይነቶች
- 1. የሰው ሽንትና ዓይነ ምድሩ
- 2. የወር አበባ ደም
- 3. ሥጋቸው የማይበላ እንስሳት ሽንትና ፋንድያ
- 4. የበከተ እንስሳ
- 5. የአሳማ ሥጋ
- 6. የውሻ ልጋግ
- 7. መዚይ
- 8. ወዲይ
- ነጃሳዎች የሚወገዱበትና የሚጸዱበት መንገድ


### የነጃሳ የቋንቋ ትርጉም

ቆሻሻ ማለት ነው።

### የነጃሳ ሸሪዓዊ ትርገም

በሸሪዓው እንዲወገድ የታዘዘ ቆሻሻ

## የነጃሳ ዓይነቶች

### 1. የሰው ሽንትና ዓይነ ምድሩ

ይህም መስጊድ ውስጥ ለሸናው ገጠሬ ሰው (አዕራቢይ) ነቢዩ ﷺ ፡- ‹‹እነዚህ መስጊዶች ለሽንትም ሆነ ለቆሻሻ ነገር የተገቡ አይደሉም፤ለአላህ ውዳሴ (ለዝክር)፣ ለሶላትና ቁርኣንን ለመቅራት ብቻ (የተገቡ) ናቸው፡፡››[1] ባሉት መሰረት ነው፡፡

### 2. የወር አበባ ደም

ኸውለህ ብንት የሳር ወደ ነቢዩ ﷺ መጥታ፡- ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ያለኝ አንድ ልብስ ብቻ ሲሆን የወር አበባዬ ይነከዋል›› ስትላቸው ነቢዩ ﷺ ፡- ‹‹ከወር አበባሽ ስትጸጂ ደም የነካውን ቦታ እጥበሽ (በልብሱ) ስገጂበት፡፡››28 አሏት፡፡

ከወር አበባ ደም ውጭ ያለው የሚፈስ (መስፉሕ)[2] ደምም ሆነ የማይፈስ ደም ንጹሕ (ጣህር) ነው፡፡ ይህም በሚከተለው ሐዲሥ መሰረት ነው፡- ‹‹ከጣዖታውያን ሙሽሪኮች አንዱ ከሙስሊሞች ሶላት በመስገድ ላይ የነበረውን አንድ ሰው በቀስት ወግቶት (ተወጊው) ፍላጻውን ነቅሎ ደሙ እየፈሰሰ መስገዱን ቀጠለበት፡፡››[3]

### 3. ሥጋቸው የማይበላ እንስሳት ሽንትና ፋንድያ

ማስረጃው ከእብን መስዑድ የተላለፈው የሚከተለው ሐዲሥ ነው፡ ‹‹ነቢዩ ﷺ ለመጸዳዳት ወጡና ሦስት ድንጋዮች እንዳመጣላቸው አዘዙኝ፤ ሁለት አግኝቼ ሦስተኛ ፈልጌ አጣሁና ፋንድያ ወስጄ አመጣሁላቸው፡፡ ሁለቱን ድንጋዮች ወሰዱና ፋንድያውን ጥለው ፡- ‹ይኸ ርክስ31 (የተነጀሰ) ነው፡፡› አሉ፡፡››[4]

(1) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ
(2) በአቡ ዳዉድ የተዘገበ
(3) መስፉሕ ደም ቦታውን ለቆ የሚፈስ ደም ነው፡፡
(4) በአቡ ዳውድ የተዘገበ

https://www.al-feqh.com/am

"
## ሥጋቸው የሚበላ እንስሳት ሽንትና እበት ብያኔ (ሑክም) ምንድነው?

ሥጋው የሚበላ እንስሳ ሽንትና እበቱ (በጠጡ) ጣህር (ንጹሕ) ነው፡፡ ከአነስ ብን ማሊክ (ረዐ) በተላለፈው መሰረት የተወሰኑ ሰዎች መዲና መጥተው እዚያ ታመሙና የግመሎቹን ሽንትና ወተት ይጠጡ ዘንድ ሰዎቹን ነቢዩ ﷺ ወደ ዘካት (ሶደቃ) ግመሎች ላኳቸው፡፡ "

## 4. የበከቱ እንስሳት

የበከተ እንስሳ ማለት ሸሪዓዊ በሆነ መንገድ ሳይታረደ የሞተ እንስሳ ነው፡፡ ይህን በማስመልከት አላህ ﷻ እንዲህ ብሏል፡-

﴿قُل لَّآ أَجِدُ فِي مَآ أُوحِيَ إِلَيَّ مُحَرَّمًا عَلَىٰ طَاعِمٖ يَطۡعَمُهُۥٓ إِلَّآ أَن يَكُونَ مَيۡتَةً أَوۡ دَمٗا مَّسۡفُوحًا أَوۡ لَحۡمَ خِنزِيرٖ فَإِنَّهُۥ رِجۡسٌ﴾ [الأنعام:145]

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው፡- ወደኔ በተወረደው ውስጥ በክት፣ፈሳሽ ደም ወይም የአሳማ ስጋ፣እርሱ ርኩስ ነውና ወይም በአመጥ ከአላህ ስም ሌላ በርሱ ላይ የተወሳበት ካልኾነ በስተቀር በሚመገበው ተመጋቢ ላይ እርም የኾነን ነገር አላገኝም፤. . . ›› [አል-አንዓም:145]፡፡ አንድ እንስሳ ሳይታረድ በሕይወት እያለ የተቆረጠ የእንስሳ አካልም በበክት ውስጥ ይጠቃለላል፡፡

የሚከተሉት ግን በዚህ ውስጥ አይካተቱም፡-

### 1. የሞተ ዓሳና አንበጣ ፡-

ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ሁለት (ዓይነት) የሞቱ እንስሳትና ሁለት (ዓይነት) ደሞች የተፈቀዱ (ሐላል) ተደርገውልናል፡፡ ሳይታረዱ ሞተው የተፈቀዱት ዓሳና አንበጣ ሲሆኑ ሁለቱ ደሞች ደግሞ ጉበትና ጣፊያ ናቸው፡፡››[1]

### 2. እንደ ዝንብ ያሉ ፈሳሽ ደም የሌላቸው የሞቱ ነፍሳት ፡-

ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ዝንብ በአንዳችሁ ዕቃ ውስጥ ሲገባበት ሙሉ በሙሉ ዝንቡን ያጥልቅበትና አውጥተው ይጣለው፤በአንድ ክንፉ ፈውስ በሌላ ክንፉ በሽታ አለበትና፡፡››[2]


የበከተ እንስሳ


ዓሳ


አንበጣ


ዝንብ

(1) በአሕመድ የተዘገበ

(2) በቡኻሪ የተዘገበ

https://www.al-feqh.com/am



## 5. የአሳማ ሥጋ

ይህን በማስመልከት አላህ ﷻ እንዲህ ብሏል፡-

﴿قُل لَّآ أَجِدُ فِي مَآ أُوحِيَ إِلَيَّ مُحَرَّمًا عَلَىٰ طَاعِمٖ يَطۡعَمُهُۥٓ إِلَّآ أَن يَكُونَ مَيۡتَةً أَوۡ دَمٗا مَّسۡفُوحًا أَوۡ لَحۡمَ خِنزِيرٖ فَإِنَّهُۥ رِجۡسٌ﴾ [الأنعام:145]

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው፡- ወደኔ በተወረደው ውስጥ በክት፣ፈሳሽ ደም ወይም የአሳማ ስጋ፣እርሱ ርኩስ ነውና ወይም በአመጥ ከአላህ ስም ሌላ በርሱ ላይ የተወሳበት ካልኾነ በስተቀር በሚመገበው ተመጋቢ ላይ እርም የኾነን ነገር አላገኝም፤. . . ››[አል-አንዓም:145]።



አሳማ

## 6. የውሻ ልጋግ

ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ያንዳችሁን ዕቃ ውሻ በአፉ (ምላሱን በማስገባት) ከለከፈው የሚጸዳው (ዕቃውን) ሰባት ጊዜ አንደኛውን ዙር በአፈር በማጠብ ነው፡፡››(1)

የውሻ መልከፍ ማለት ቢጠጣም ባይጠጣም በዕቃዎች ውስጥ ምላሱን አስገብቶ የመነካካቱ ሁኔታ ነው፡፡



የውሻ ልጋግ (በምላሱ መልከፍ)

## 7. መዚይ

መዚይ ስለ ሩካቤ ሥጋ በማሰብ ወይም ከተቃራኒ ጾታ ጋር በመነካካትና በመተሻሸት ምክንያት ከብልት የሚወጣ ነጣ ያለና የመጣበቅ ባህሪ ያለው ፈሳሽ ነው፡ ሲወጣ የእርካታ ስሜት የማፈጥርና የማይደፍቅ ሲሆን ከወጣ በኋላም የመለዘብ ስሜት አያሳድርም፡ ምናልባትም ሲወጣ ለሰውየው ምንም ላይሰማው ይችላል፡፡

ነቢዩ ﷺ ዐሊይ ብን አቡ ጧሊብ (ረዐ) ስለ መዚይ ሲጠይቋቸው እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ዉዱእ አድርግ፤ብልትህንም ታጠብ፡፡››(2)

## 8. ወዲይ

ወዲይ ከውሃ ሽንት በኋላ ከብልት የሚወጣ ወፈር ያለ ነጭ ፈሳሽ ነው፡፡



(1) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ

(2) በሙስሊም የተዘገበ



https://www.al-feqh.com/am

https://www.al-feqh.com/am



https://www.al-feqh.com/am

## መኒይ ንጹሕ (ጣህር) መሆኑ

መኒይ (ወንዴ የዘር ፈሳሽ) ስሜት በሚሰጥ ሁኔታ ከብልት የሚደፈቅና ከወጣ በኋላ የመሟሸሽ ሁኔታ የሚከተለው ነጭ ወፍራም ፈሳሽ ነው። የተምር እሸት ጠረን ያለው ሲሆን ከስንዴ ሊጥ ጠረን የቀረበ ነው።

መኒይ ጣህር ነው፤ነጃሳ ቢሆን ኖሮ ነቢዩ ﷺ እንዲታጠብ ባዘዙ ነበር።

መኒይ እርጥብ ከሆነ በውሃ ማጠብ ደርቆ ከሆነ ደግሞ በመፈግፈግ ማስወገድ በቂ ነው። ከዓእሻ (ረዐ) በተላለፈው መሰረት

‹‹የአላህ መልእክተኛ ﷺ መኒይ የነካውን ልብስ አጥበው የታጠበውን ቦታ (እርጥበቱን ) በዓይኔ እያየሁ በዚያው ልብስ ለሶላት ይሄዱ ነበር።››[1] ብለዋል። በሙስሊም ዘገባ ደግሞ ‹‹ከአላህ መልእክተኛ ﷺ ልብስ ላይ በሚገባ ፈግፍጌ በዚያው ይሰግዱ ነበር።››[2] የሚል ተመልክቷል።



እርጥብ ከሆነ ማጠብ



ደረቅ ከሆነ መፈግፈግ

(1) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ
(2) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ

## አልኮል

አልኮል ሕሊናዊ እርኩስነቱና ነጃሳነቱ፣ መጠጣቱ ደግሞ ከከባዳ ኃጢአቶች አንዱ መሆኑ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ቁሳዊ ነጃሳነት የሌለው ጣህር ነው።

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِنَّمَا ٱلۡخَمۡرُ وَٱلۡمَيۡسِرُ وَٱلۡأَنصَابُ وَٱلۡأَزۡلَٰمُ رِجۡسٞ مِّنۡ عَمَلِ ٱلشَّيۡطَٰنِ فَٱجۡتَنِبُوهُ لَعَلَّكُمۡ تُفۡلِحُونَ ٩٠﴾ [المائدة:90]

‹‹እላንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ፣ቁማርም፣ጣዖታትም፣አዝላምም (የመጠንቆያ እንጨቶች) ከሰይጣን ሥራ የሆኑ እርኩሶች ብቻ ናቸው፤(እርኩስን)

ራቁት፤ልትድኑ ይከጀላልና።››

[አል-ማኢዳህ:145]። በሚለው የአላህ ﷻ ቃል ውስጥ የተመለከተው ርክሰት ቁማርና ጣዖታትንም (መይስር[1] እና አንሷብ[2]) የሚያካትተው ሕሊናዊ ርክሰት እንጂ አካላዊና ቁሳዊ ነጃሳነት አይደለም።




አስካሪ መጠጦች

(1) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ
(2) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ

https://www.al-feqh.com/am



## ነጃሳዎችን የማስወገጃ መንገዶች

### 1. መሬትን ከነጃሳ የሚጸዱበት መንድ

መሬት ነጃሳ ከነካው በውሃም ይሁን ወይም በሌላ ነገር ነጃሳው ይወገዳል። መስጊድ ውስጥ የሸናውን ገጠሬ ዐረብ አስመልክተው ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋልና፡ ‹‹ተውት (ሰውየውን አትንኩት)፤ በሸናበት ቦታ ላይ

ባልዲ ሙሉ[(1)] ወይም በትልቅ ባልዲ[(2)] ውሃ ድፉበት[(3)]።››[(4)]

መሬቱን የበከለው ፈሳሽ ነጃሳ ከሆነ በመድረቁ ብቻ መሬቱ የጸዳ ይሆናል። ይህም ከአቡ ቀላባ በተላለፈውና ፡-‹‹መሬት ከደረቀ ጣህር[(5)] ሆኗል።››[(6)]



የውሃን መጠን በመጨመር ማጽዳት



ፈሳሽ ነጃሳ መሬት ላይ

(1) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ
(2) በቡኻሪ የተዘገበ
(3) በሙስሊም የተዘገበ
(4) በአቡ ዳዉድ የተዘገበ
(5) በአቡ ዳዉድ የተዘገበ
(6) በአቡ ዳዉድ የተዘገበ



የፈሳሽ ነጃሳ መድረቅ

### 2. የተነጀሰ ውሃ የሚጸዱበት መንገድ

ነጃሳ የገባበት ውሃ ቅሪቱ እንዲወገድ የበዛ ውሃ በመጨመር ይጸዳል። በዘመናዊ የማጥሪያ ዘዴዎችም ሊጠራ ይችላል።



በዘመናዊ ዘዴዎች ማጽዳት



የውሃን መጠን በመጨመር ማጽዳት

### 3. የተነጀሰ ልብስ የሚጸዱበት መንገድ

ነጃሳው እስኪወገድ ድረስ በውሃ ፈግፍጎ በማጠብና በመጭመቅ ይጸዳል።



የተነጀሰ ልብስ የሚጸዱበት መንገድ



https://www.al-feqh.com/am

https://www.al-feqh.com/am



https://www.al-feqh.com/am

## 4. ምንጣፍ ከነጃሳ የሚጸዱበት መንገድ

ነጃሳው እስኪወገድ ድረስ በውሃ ይታጠባል፤፤ወይም በዘመናዊ ማጽጃዎች በመፈግፈግም ይጸዳል።



ምንጣፍ የሚጸዱበት መንገድ

## 5. የሞተ እንሳሳ የሚጸዱበት መንገድ

### 1. ሥጋው የሚበላ እንስሳ ቆዳ ፡-

ይህ ቆዳውን ከውስጥና ከውጭ በኩል በማልፋት ከነጃሳ ይጸዳል። ይህም በሚከተለው የነቢዩ ﷺ ሐዲስ መሰረት ነው፡- ‹‹ቆዳ ከተለፋ ንጹሕ (ጣሀር) ሆኗል።››(1)

ቆዳ መልፋት ማለት ቆዳው ለስልሶ መጥፎ ጠረኑ እስኪወገድ ድረስ የተወሰኑ ኬሚካሎችን በመጠቀም ማዘጋጀት ማለት ነው።



ቆዳን ማልፋት



ሥጋው የሚበላ እንስሳ

ሥጋው የሚበላ እንስሳ በሸሪዓዊ መንገድ ታርዶ ከሞተ ግን ቆዳው ጣህር ነው።

### 2. የበከተ ሥጋው የማይበላ እንስሳ ቆዳ፡

በሕይወት እያለ በቁሙ ጣህር ቢሆን እንኳ ፤በሸሪዓዊ መንገድ መታረዱ ሐላል የማይሆነው እንስሳ ቆዳ ቢለፋም ንጹሕ (ጣህር) አይሆንም።



ሥጋው የማይበላ እንስሳ

## 6. ምግብ መብላት ያልጀመረ ወንድ ወይም ሴት ሕጻን ሽንት የሚጸዱበት መንገድ

የሴት ሕጻን ሽንት ይታጠባል። የወንድ ሕጻን ሽንት ግን ላዩ ላይ ውሃ ማፍሰስ ብቻ በቂ ይሆናል። ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋልና ፡- ‹‹የሴት ሕጻን ሽንት ይታጠባል፤የወንድ ሕጻን ሽንት ውሃ ይረጭበታል።››(2)



የወንድ ሕጻን ሽንትን ውሃ ላዩ ላይ መርጨት

(1) በአቡ ዳዉድ የተዘገበ

(2) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ

https://www.al-feqh.com/am



የሴት ሕጻን ሽንትን ማጠብ

## 7. ውሻ የለከፈው ነገር የሚጸዱበት መንገድ

ውሻ በአፉና በምላሱ የነካውን ነገር ሰባት ጊዚ አንደኛውን በአፈር በማጠብ ይጸዳል፡፡ ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ያንዳችሁን ዕቃ ውሻ በአፉ (ምላሱን በማስገባት) ከለከፈው የሚጸዳው (ዕቃውን) ሰባት ጊዜ አንደኛውን ዙር በአፈር በማጠብ ነው፡፡››[1]

አንድ ጊዜ | 6 ጊዜ




በአፈር ማጽዳት | በእጥበት ማጽዳት

## 8. መዚይና ወዲይ የሚጸዱበት መንገድ

ብልትን በማጠብና ዉዱእ በማድረግ፡ ነቢዩ ﷺ ዐሊይ ብን አቡ ጧሊብ (ረዐ) ስለ መዚይ ሲጠይቋቸው እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ዉዱእ አድርግ፤ብልትህንም ታጠብ፡፡››[2]

መዚይ ወይም ወዲይ የነካውን ልብስ በተመለከተ በነኩት ቦታ ላይ ውሃ በመርጨት ይጸዳል፡ ሰህል ብን ሐኒፍ ባስተላለፉት ሐዲስ፡- ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ልብሴን የነካውን እንዴት አደርጋለሁ ስላቸው እፍኝ ውሃ ወስደህ ነክቶት ባየህበት የልብሱ ቦታ ላይ መርጨት ብቻ በቂህ ነው አሉኝ፡፡››[3] ብለዋል፡፡

(1) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ
(2) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ
(3) በአቡ ዳዉድ የተዘገበበ

## 9. የወር አበባ ደም የሚጸዱበት መንገድ

በውሃ በማጠብ ይጸዳል፡፡ የቅሪቱ መኖር ችግር አይኖረውም፤ነቢዩ ﷺ ፦ ‹‹ውሃ ይበቃሻል፤የቅሪቱ መኖር ችግር የለውም፡፡››[4] ብለዋልና፡፡

## 10. ጫማ የሚጸዱበት መንገድ

የነጃሳው ቅሪት እስኪወገድ ድረስ መሬት ላይ በመፈግፈግ ይጸዳል፡፡ ነቢዩ ﷺ ፦ ‹‹አንዳችሁ በጫማው አዋኪ ነገር ከረገጠ አፈር (የነጃሳ) መጽጃው ነው፡፡››[5] ብለዋል፡፡



ጫማን መሬት ላይ በመጥረግ ማጽዳት

## 11. የሴት ረዥም ልብስ የሚጸዱበት መንገድ

ረዥም የሴት ቀሚስ በጫፉ ላይ ነጃሳ ቢጣበቅበት ንጹሕ በሆነው ቦታ መሄዷ ይበቃታል፤መሬቱ ራሱ ያጸዳዋልና፡፡ ነቢዩ ﷺ ፦ ‹‹ከኋላው ያለው ያጸዳዋል፡፡››[6] ብለዋል፡፡



መሬት የሴትን ልብስ ያጸዳል

(4) አቡ ዳዉድ የተዘገበ
(5) በአቡ ዳዉድ የተዘገበ
(6) በአቡ ዳዉድ የተዘገበ

## 12. ጠጣር ምግቦች የሚጸዱበት መንገድ

ነጃሳው ያለበትንና በዙሪያው ያለውን በማስወገድ ይጸዳል። ቀሪው በመሰረታዊ ንጽሕናው ላይ እንዳለ ይቀራል። የአላህ መልእክተኛ ﷺ :- ‹‹ቅቤ ውስጥ ስለ ወደቀች አይጥ ተጠይቀው ‹‹አስወጧትና በዙሪያዋ ያለውን አስወግዳችሁ ቅቤያችሁን ተመገቡ።››[1] ብለዋል፡ ፡



አይጥ ገብቶ የሞተበት ቅቤ

## 13. እንደ መስተዋትና ብርጭቆ ያሉ የጠሩ ገጾች የሚጸዱበት መንገድ

የነጃሳው ቅሪት እስኪወገድ ድረስ ይወለወላል።



መስተዋት በመወልወል ይጸዳል

(1) በቡኻሪ የተዘገበ

## ነጃሳዎችን የሚመለከቱ ጠቃሚ ነጥቦች

1. ነጃሳ መሆናቸውን የሚያስረዳ ነገር እስካልቀረበ ድረስ ነገሮች ሁሉ በመሰረቱ ንጹሕ (ጣህር) ናቸው።
2. በአንድ ነገር ላይ ነጃሳ ከወደቀና የነካው ቦታ ተለይቶ ያልታወቀ ከሆነ ሙሉ በሙሉ ይታጠባል።
3. ነጃሳ በሆነ ነገር ውስጥ ሟምቶ ከተዋሐደው - ለምሳሌ ያህል የአህያ ፋንድያ ተቃጥሎ ወደ አመድነት ቢለወጥ - በዚሁ ይጸዳል።



ፋንድያ ወደ አመድነት ሲለወጥ የጸዳ ያደርገዋል

https://www.al-feqh.com/am